# ዝክረ-ታሪክ



## የሮሙ አርበኛ

# ከነበሩት፣ ካሉት

ከመላኩ ይስማው

ኤርትራ፣ ሰራዬ አውራጃ ውስጥ አዲሃይሰ በተባለችው ቀበሌ በ1908 ዓ. ም. ተወለደ። በወቅቱ ኤርትን ከተቀረዉ የኢትዮድያ አካልቆርሰዉ በመያዝ ይገዙ የነበሩት ጣሊያኖች ካቶሊካዊ ትምህርት ቤቶችን በየቦታዉ በመክፈት የዚያን አካባቢ ህጻናትና ወጣቶች ስነ-ልቦና የመስለብ ጥረታቸዉን አጠናክረዉ ነበር። ከነኝሁ በአንዱ ትምህርቱን ለተከታተለዉ ለዚህ ወጣት ግን የተጠቀሰዉ የጣሊያኖች ጥረት ኢትዮድያዊነቱን ይበልጥ እንዲያውቀው፣ ይበልጥ እንዲያጠብቀዉ አደረገዉ።

ትምህርቱን እንደጨረሰ (በጊዜው ጠላት መላ ኢትዮጵያን ወርሮ ነበር) ባስተማሪነት እንዲሰራ የተላከዉ ኮረም ወደተባለው ቦታ ነበር። በግሉ ደግሞ ሰሊትዮጵያዊነት መህምርነቱን ተያያዘው። በድብቅ እያዘጋጀ ለጉዋደኞቹና ለወጣቶች ይበትን የነበረው ጽሁፍም ለዚህ አስረጂ ነው። ከበተናቸው ጽሁፎች አንዱ ለምሳሌ፦

«እኛ ኢትዮጵያዊያን እንጂ ጣሊያናዊ አይደለንም። በኢትዮጵያዊነታችን ብዙ የሚያኰራን ታሪክ አለን። ዓለምን የሚያስቀና ዘርና ሃገር አለን። የኛ መነጣጠል ግን ለጠላት መመቸት ነው። በራሱ ታሪክ፣ በራሱ ሃገር የማይተማመን ዜጋ በጠፈር ላይ የተበተነ ዱቄት ይመስላል። መማር፣ ማንበብና ፣ መጻፍ በይበልጥ አገርንና ወገንን ለመውደድ እንዲያበቃ እንጅ አጉል ጥራዝ ነጠቅ ሆነን ላገራችን ሸክምና በሽታ ልንሆንባት አይገባም» ይላል።

ባዕዳኑ ወንጌላዊያን የወገንን ስነ-ልቦና ለማዳሸቅ የተገለገሉበትን «መንፈሳዊ» አቀራረብ በመጠቀም ም ጠላትን ታግሏል -ወጣቱ። ይኸውም ኢትዮጵያ በጠላት እጅ ወድቃለችና ከኢትዮጵያዊያን ወንድሞቻችን ጐን እንሰለፍ በሚል ዓላማ የተመሰረተውን የ«ገብረ-ሚካኤላዊያን» ማህበር በፕሬዚዳንትነት በመምራት ነበር። በዚህ በዚህ መልክ ጠላትን እየተፋለመ ሳለ በሮም የአርበኝነት ውሎውን እንዲፈጽም ራሱ ለራሱ ቃለ-መሃላ ያስገባው አንድ ሁኔታ አጋጠመው።

ዓመቱ 1928፣ ወሩ ሐምሌ ነበር። በወቅቱ የመቀሌ ገዢ የነበረው ኮማንዳቶሪ እስኩድሪ የተባለው ፋሽስት ወደ ሮም ሲሄድ እግረ-መንገዱን አስመራ ጐራ ብሎ አንድ ጐራዴ ይዞ ከተማ ውስጥ ሲንጐራደድ ያያል _ ወጣቱ። አዋቂዎችን ሲጠይቅ ጀግናው አሉላ አባነጋ ዶጋሊ ላይ ጣሊያኖችን ድል የመቱበት ጐራዴ ከጠላት እጅ ገብቶ መሆኑን ይነግሩታል። ይህን ጊዜ እራሱ ለረሱ ቃል ገባ - ያባት አርበኛውን ጐራዴ ከጠላት አጅ በማውጣት ክብር ሊያጎናጽፋት። ይህንኑ ውጥኑን ያማከረው ወንድሙ ለጉዳዩ ክብደት ሳይሰጠው ቸል ሲልም፣

«ብረት ሁሉ ብረት አለመሆኑን ከድንጋይ እንኳን የተመረጠ ድንጋይ መኖሩን አትዘንጋ። ጣሊያኖች ከጐራዴ ለይተው ሮማ የወሰዷት የተለየች ስለሆነችና ታሪከኛ መሆኗን አውቀው ነው። ሁልጊዜም አንድ አገር በሌላው ሲወረር ከተወረረችው አገር ውስጥ አስቀድሞ የሚሄድ የታሪክ ዕቃ ነው። ይኸውም ታሪክን ለማጥፋት ከሚታሰበው ብርቱ ባለጋራነት የተነሳ መሆኑን ልታውቀው ይገባል። ስለዚህ ነው የታሪክ መታሰቢያ ከሌለን ታሪካችን ይጠፋል የምልህ።» ነበር ያለው።

አርበኛው ወጣት እንደምን አድርጎ ጐራዴውን ከጁ እንደሚያስገባ ሲያወጣ ሲያወርድ ለዚሁ የሚረዳ ሁኔታ አጋጠመው። ሮም ውስጥ ባሰተርጓሚነት የሚያገለግል ሰው አስፈልጎና እሱም ስለብቃቱ በቀድሞ አስተማሪዎቹ ታምኖበት ወደዚያው መላኩ ነበር ውጥኑን ተግባራዊ ለማድረግ ጊዜው መቃረቡን ያበሰረው አጋጣሚ።



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ሮም ከሄደም በኋላ የራስ አሉላን ክቡር ጐራዴ ከጁ ለማስገባት ማድባቱን ቀጠለ። ሮም በቆየበት ወቅት በልቦናው ምን ያስብ እንደነበር የጓደኛውን ባንዳ መሆን በሰማ ጊዜ ለወንድሙ ለተስፋጽዮን የጻፈው የከዚህ በታቹ ደብዳቤ በግልጽ ይመሰክራል፥

«ማንኛውም ፍጡር ወላጁን መስሎ ነው የሚወጣው፣ ለምሳሌ ዝንጀሮ ጦጣን መውለድ አትችልም። ጦጣም ነብርን ወይም አነርን መውለድ አይቻላትም። ሌላውም ፍጡር ሁሉ እንደዚሁ ነው። አባቶቻችን በምሳሌ ሲሰድቡ «መሬት ሲያረጅ መጭ ያበቅላል» ይላሉ፤ እነሱ በኩራትና በክብር በደማቸውና በአጥንታቸው የገነቡትን ነጻነት እኛ ዛሬ እንሻሻጥበታለን፤ ያሳዝናል፤ ወይ አልቀደምን ወይንም ወደኋላ አልቀረን፤ በመሃል ቤት ተፈጥረን በመንፈስ እንሰቃያለን፤ ገብረዓብ የሰራኝን ሰምተህ አንተም ስለጉዳዩ ጽፈኸልኛል፤ ሃዘኑ የኔ ብቻ ሳይሆን አገሩንና ወገኑን ለሚወድ ሁሉ ይተርፈዋል፤ እኛ ዛሬ ልጆች አይደለንም፤ ብሔራዊ ፍቅርና አንድነታችንን ማጥናት አለብን፤ ለዕለት ሆዳችን መለወጥ የለብንም።፤ ጠላቶቻችንም የኛን መነጣጠል ስለሆነ የሚሹት ይኸው ያዘላቸው። እኔ ወንድሜ ወገኔነው ብዬ ለአንድነታችን የሚጠቅም ሃሳብ ብጽፍለት እስከዚህ አሳልፎ እንዴት ይሰጠኛል? ለመሆኑ ሌላ ከበድ ያለ ምስጢር ብጽፍለት ኖሮ ያለፍርድ አሰቅሎኝ ነበር ማለት አይደለንም? ያሳዝናል፤ በእውነቱ እልሃለሁ፤ ዛሬ እኛ ተማርን ብለን ከምንመጻደቀው ወጣቶች ይልቅ ከኛ በፊትም ሆነ አሁን በቅን ሳገራቸው የሚሰየፉት መሃይምኖች በጣም ይበልጡናል።

አሁን ለምሳሌ ከሃማሴንና ከጠቅላላው ኤርትራ ግዛት ከኢጣሊያ እያመለጡ ከአርበኞች ጋር ተቀላቅለው ለክብራቸውና ለነጻነታቸው በዱረ በገደል ሰቃይን የሚቀበሉት ህዝቦች ቁጥራቸው ብዙ ነው። የናቴን መሰቃየት እያሰበኩ ለስም የሚሆን ነገር ሳላተርፍላት እያልኩ እንጂ ሆዴ ፍጹም እየበረደው ለመኖር አልመርጥም ነበር። ስለዚህም አቅጣኝና አፍጣኝ እመዳሮው ላይ እንገናኝ እንደሚባለው አነጋገር ሁሉ እኔ ለማን እንደማስብ እነሱም ለማን እንደሚያስቡ አንድ ቀን መለየቱ የማይቀር ነው። ለማንኛውም በቅርብ እመጣለሁ።

ይኸውና ልመለስ እያልኩ ስለምን ብዙ ጊዜ ሆነኝ። አየሩ አልተስማማኝምና ወደአገሬ ሄጄ ትንሽ አየር ልለውጥ ብዬ አለቃዬን በመለመን ላይ ነኝ።

እኔና ገብረ-አብ ዓይን ለዓይን መተያየታችን አይቀርም። በኢትዮጵያ ላይ በአይነ-ህሊናህ ሆነህ የምታየው ግፍ ቃላቶች አይዘረዝሩትም። ከሁሉም የሚነደኝ ከመሃል ኢትዮጵያ ድረስ እየመጡ በወገናቸዉና በሀገራቸው ላይ የሚቀላምዱትን የኢጣሊያ ደጃዝማቾች ስሰማና ሳይ ነው። እኔ በነገር ብቻ ሳምባዬ አረረ፤ አሁንስ በጣም ነው የመረረኝ።

ከነሱ የማገኘው ክብርና ጸጋ ሁሉ ሰውነቴን እንደ ዶሮ ቅንቅን ሲበላኝ ነው የሚያደረው፤ ለማንኛውም ሃሳቤ እንደተሳካልኝ እመጣለሁ፤ ያቺንም ጐራዴ አግኝቻታለሁ፤ ግን እጄ አልገባችም። ስለ ጐራዴዋ ስነግርህ እንደምትደነግጥ ይሰማኛል፤ ግን በልዩ ዘዴ አመጣታለሁ፤ አትስጋ። ይህንማ ካላደረግሁ ጨርሶ የኢጣሊያ መሳሪያ ነኝ ማለት ነው።

በል እንግዲህ ለገብረ-አብ ከእንግዲህ እስላምና ክርስቲያን መሆናችንን እንዲያውቀው ንገረው፤ ባል ሲኪም ሁኔታውን እንደሚነግረው አውቃለሁ።

ግን እኔ ስመጣ ወደኔ ተለጥፎ ለመቀላመድ እንዳይችል አስጠንቅቀው። በኋላ ጉድ እንዳይፈላበት። ከአሁን በኋላ እንደዚህ ባሉት ሃማሴን ጐሳዎች ላይ ሌላ እርምጃ ነው የምወስደው። እናታችን እንዳትሰጋ ስለማንኛውም ነገር አትንገራት፤ በል ደህና ሁን።» ነው የሚለው የታሪካዊው ደብዳቤ ሙሉ ቃል።

ከሄደበት ጊዜ ጀምሮም ከአገር ውስጥ አርበኞች ጋር የሚያደርገውን ግንኙነት አላቋረጠም ነበር። ስረፍት ወደሀገሩ ለመመለስ ፈቃድ ባገኘ ጊዜ ባቀረበው ጥያቄ መሰረት የዘወትር ጥማቱ የነበረውን ያሉላ አባ-ነጋ ጐራዴ ለኮማንዳቶሪው መልሶ ያደርስለት ዘንድ ከስምምነት ላይ ተደረሰ። ከዚህ በኋላ ዕቃውን በባቡር ለማስጫን እየተዘጋጀ ሳለ፣ በስምምነቱ መሰረት ኢትዮጵያ ሳለው የፋሽስት ባለስልጣን መልሶ እንዲያደርስ የተቀበለውን ጐራዴ ታጥቆ፣ ሌላ ጠላት ዘርፎ ወደሮም ወስዶት የነበረ የታሪክ ቅርስ ለመሰናበት ወደሮም ፒያሳ ሄደ። ቅርሱም የይሁዳ አንበሳ ምስል ነበር። ዘራፊው ጠላት አንበሳው ላይ የተኩላ ምስል አስቀምጦበታል። እላዩ ላይ የተጻፈውንና«ልጆችሽ የይሁዳ አንበሳ እየተባለ በቃለ-አጋኖ ሲወራለት የነበረውን ከሃገሩ እንደፍዬል ጭራውን ጠምዝዘው አምጥተው ከግርሽ ስር ያሰግዱታል» የሚለውን መራር ጥቅስ አነበበ - ወጣቱ። ባካባቢው የተሰበሰበው ህዝብም እየጮኸና በየተራ ካንበሳው ላይ እየወጣ «ብላ! የተራብከው አንበሳ ከድህነት አመጣንህ! ምግብ ሞ



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ልቱዋል፣ ሆድህን እየሞላህ ማገገም አለብህ! ....» በማለት ዳቦ ባፉ ውስጥ እየጨመረ ሲሳለቅበት አስተዋለ - ውስጡ በንደት እየተቃጠለ። ወደ አንበሳው በመሄድም ተንበረከከና ይፀልይ ጀመር።

በመካከሉ የከተማዋን ፀጥታ ሲቆጣጠር የነበረው ማርሻል ማረዴ ሻምላ ከያዙ ሶስት አጃቢዎቹ ጋር ሆኖ ወጣቱ ወደነበረበት ስፍራ መጣ። ማርሻሉም ወደወጣቱ በመቅረብ «አንተ እንድታይ ማን ፈቀደልህ?!» በማለት ተንበርክኮ ከሚፀልይበት ሊያስነሳው ሞከረ። የፋሽስቱ ባለስልጣን፣

«ምን ያደርግልሃል!? ከንግዲህ አንበሳ የሚባል የለም! ይልቅስ ለመቤቲቱ ለተኩላ ስገድ!» በማለት ሲሳለቅበት የዕለቱ ትእይንት መጋረጃ ተከፈተ። በወጣቱ አርበኛነት፣ የራስ አሉላ አባ-ነጋ ጐራዴ ጠሳትን ዳግም ታጭድ ጀመር- ጣሊያን፣ ሮም ውስጥ! ሲሳለቅበት የሞከረውን ማረሻል ማረዴንንም ለአንበሳው ካሰገደው በኋላ በታጠቀው ጐራዴ ቆራርጦ ጣለው። በጠቅላላው አምስት የጣሊያን ፋሽስት ባለስልጣኖችን በዚያ ጐራዴ ሰየፈበት።

ህዝቡ ጩኸቱን ለቀቀው። ሮም ተናወጠች። «ኢትዮጵያ ጠላታችን ከተማችንን ሰብራ ገብታለችና መሳሪያ ያለህ በመሳሪያህ፣ የሌለህ ከመጋዘን እያወጣህ ለነፃነትህና ለክብርህ ቶሎ ገብተህ ተከላከል።» የሚል መልእክት ያለው አዋጅ ከሞሶሎኒ መንግስት ተነገረ። ተኩሱ ቀለጠ። ጣሊያን እርስ በርሱ ተፋጀ። ከዚህ ሁሉ በኋላ በመጨረሻ ላይ እግሩን በጥይት ተመትቶ የተያዘው የጣሊያን ጠላት ግን ብቸኛውና ኢትዮጵያዊው ያ ወጣት ነበር! ጠላት ውርደቱን ለመሸፈን እብድ ነው ብሎ አስወራበት። እብድ ብለው ለፍርድ ሮም ውስጥ እህዝብ ፊት ሲያቀርቡት፦

«እኔ ሙሉ ጤነኛ ነኝ፤ ያለእናንተ በስተቀር ምንም በሽታ የማያውቀኝ የሃያ ሁለት አመት ሰው ነኝ። ጥዋት ማታ በየመናፈሻው በየአደባባዩ በየፎቁ ላይ እየሆናችሁ «ሮማ ሮማ ኢጣሊያ ኢጣሊያ» በማለት የምታናግሯት አገራችሁ ሰለሆነች ነው። ያገርን መውደድ ቋንቋ ካወቃችሁ እኛስ አገራችንን እንድንጠላ እርስበርሳችን ተጣልተን መንግስታችንን እንድንረሳ ለምን ታስገድዱናላችሁ?

ዛሬ የኢጣሊያንን ወታደሮች ገድለሃል ህዝቡም በአንተ ረብሻ የተነሳ አልቋል። አመድህ በመላ የሮማ ግዛት በነፋስ መበተን አለብህ በሚል ክስ ተከሰሼ በዚሁ አደባባይ ቀርቤያለሁ። ...እኔን ለመፋረድ ከሺህ ህዝብ በላይ እነሆ ተሰብስቦ ይታያል። የፋሽስት ወሮበሎች በአገሬ ውስጥ ተሰደው በሚሊዮን በሚቆጠሩ ህፃናትና ሽማግሌ ጐልማሳና ኮረዳ በጥይት በመርዝ ጢስ፣ በእሳት በገደል ባካፋ በዶማ እየተጨፈጨፉ እየተፈለጡ ያለቁት ሁሉ የሚፋረዱት የት ይሆን? የሚፋረዳቸው ማን ይሆን? ግን የነሱ አጥንትና ደም ዋጋ ሲኖረው የናንተ ሰም እየገማ መሄዱን ዛሬ አይታያችሁም። ...አሁንም ለመጨረሻ የምናገረው የኢጣሊያ ባንዴራ ይውደቅ! የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በታላቅ ክብር ትኑር! ንጉስ ተፈሪ በድል አድራጊነት ይኑር! የይሁድ አንበሳ ምን ጊዜም ድል ከሱ ይሁን!» አሳቸው። አርበኛው ወጣት ኢትዮጵያዊ እዚያው ጣሊያን አገር፣ ባንድ የደሴት እስር ቤት ውስጥ እንዳለም በተወለድ በ29 ዓመቱ አረፈ።

ጠላት ከተባረረ በኋላም የአርበኘነት ገድሉን ለመዘከር ሀውልት እንዲሁም መፅሀፍ ወጥቶለታል። ከድል በኋላ የተቋቋመው የኢትዮጵያ ባህር ኃይል የመጀመሪ ጦር መርከብም የተሰየመችው በሱ ስም ነበር። **ዘርዓይ ደረሰ፣ የወንዶች ወንድ / ሮማ ገብቶ ጣሊያን የሚያርድ!** የሚለው ኪናዊ ሀውልትም በአማርኛው ስነ-ቃል ውስጥ ጎልቶ ይደመጥለታል። ዘርዓይ ድረሰ - ኢትዮጵያዊው አርበኛ።

(ምንጭ፦ ከ ሩሕ፥ ቅጽ 1፣ ቁጥር 8፣ ህዳር 1985 ላቀራረብ በሚያመች መልኩ ተጨምቆ የተወሰደ)



PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com